# ምንሽሮ

እመቤት ተሾመ ከበደ



# ምንሽሮ

(አጫጭር ተረኮች)

እመቤት ተሾመ ከበደ

2014 ዓ.ም

© የጸሐፊዋ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
የመጀመሪያ እትም - ሐምሌ 2014 ዓ.ም

አርታኢዎች፡-

ዘመዱ ደምስስ - (የውጭ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ መምህር፣ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ)

እንግዳወርቅ እንድሪያስ - (የሥነ ጽሑፍ መምህር፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ)

የገጽ ቅንብር እና የሽፋን ሥዕል - አዛርየስ ደሴ

# ዋና ምስጋና

ከጽንሰት እስከ ሞት ብቻ ሳይሆን ከሞት በኋላም ጭምር ተስፋ ለሚሰጥ አምላክ ምስጋና ይገባል።

ሕይወቴ ተጀምሮ እዚህ እስኪደርስ ድረስ በፍቅርና በተስፋ ለከበባችሁኝ፤ ነጻነትን ከኃላፊነት ጋር አስማምቼ እንድኖር ለረዳችሁኝ ቤተሰቦቼ፣ ጓደኞቼ እና ወዳጆቼ ምስጋና ይገባል።

መንገድ ዳር ወድቄ ባገኛችሁኝ ጊዜ ሁሉ ደግ ሳምራዊ ለሆናችሁልኝ በርካታ አልፎ ሂያጅ ግለሰቦች እንዲሁ ምስጋና ይገባል።

ሙሉ መጽሐፉን ወይም የተወሰኑ ታሪኮችን በማንበብ እና አስተያየት በመስጠት፤ እንዲሁም ፊደል በማረም ለተባበሩኝ የቅን ልብ ባለቤቶች ለሆኑት ዶ/ር አራጌ ይመር፣ በእውቀቱ ስዩም፣ ሊዲያ ተስፋዬ፣ ኪዳኔ መካሻ፣ ሜሪ ፈለቀ፣ እጸገነት ከበደ፣ ጋሻዬ ጤናው፣ ቀሉስ ተሾመ፣ መክሊት ተሾመ እና ሊና ኑሩ ምስጋናዬ እና አክብሮቴ የላቀ ነው። ብድራታችሁ አይጠፋም፤ ተባረኩልኝ።

# ልዩ ምስጋና

ለወ/ሮ ወርቅነሽ ከበደ፡-

ሙሉ ቤተሰቡ መኘታዬን ችሎ፣ ቀለቤን ሰፍሮ፣ ይኸም ሳይበቃው "ምን ጎደለ?" እያለ እጥፍ ዘርጋ ሲል ከረመ። እንደ ረድኤት ተረፈ "ክፉ አያግኛችሁ፤ ቸር አይለፋችሁ!" ማለት ወደድኩ።

ለዶ/ር አዲስ ተሾመ፡-

እናንተ ውስጥ ያለው መልካም ነገር ሁሉ የሚታየው፤ የሚችለው ነገር ካለ ሊያደርግላችሁ ለአፍታ የማያመነታ ሰው ነው። ወንድሜ ዕድሜህ ይርዘም! ልብሕን ሀዘን አይወቀው!

ለወ/ሮ አበባየሁ ደስታ (ጌጤ)፦

ያደረግሽልኝን ነገር ዘርዝሬ ባመሰግንሽ እንደምትቀየሚኝ አውቃለሁ። እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ! አመሰግናለሁ።

ለሮማን ተወልደ፦

በ11ኛው ሰዓት ድንገት ተከስታ ሁሉን ያስማመረች ደግ እና ቅን ሴት ናት። አብዝታችሁ አመሰግኗት። መጽሐፍ በማሳተም ሂደት ውስጥ ያላችሁ እና የቸገራችሁ ደግሞ ጠጋ በሏት።

ለአዛርያስ ደሱ፦

በሽፋን ምስል እና በገጽ ቅንብር ሥራ ሂደት ውስጥ እንደ ታናሽ ወንድም ነው የታዘዝከኝ። ተባረክ! እንጀራህ ሰፊ ይሁን!

# መግቢያ

የእኔ ትውልድ ዲሞክራሲ እና ሰብዓዊ መብት ከሚባሉ ግዙፍ ሐሳቦች ጋር የሚታገል መከረኛ ትውልድ ነው፡፡ እነዚህን ሐሳቦች ከብሔር ፖለቲካ ጋር አዋህዶ የያዘ ዘመናዊ 'ፍትሐ ነገሥት' ተዘጋጅቶ ተሰጥቶታል፡፡ 'ፍትሐ ነገሥቱን' እንደ ትኩስ ድንች እጁ ላይ ያገላብጠዋል፡፡ ምን እንደሚያደርገው ገና አልወሰነም፡፡

... ሁለት መብቶች የበለጠ ትርጉም ይሰጡኛል፡፡ እነሱም በሕይወት የመኖር መብት እና የኅሊና ነጻነት ናቸው፡፡ ጠዋትና ማታ የሚገደል ሰው በበዛበት ማኅበረሰብ ውስጥ ስለ ሌሎች በርካታ መብቶች መጨነቅ ምን ይጠቅማል? የኅሊና ነጻነት በሌለው ማኅበረሰብ ውስጥ ስለ ለውጥ እና ስለ ብልጽግና ማውራትስ ምን ትርጉም ያስገኛል? እነዚህ ሁለት መብቶች እንደ ባሕር ቢሆኑም፣ ቢያንስ ከመግደል እና ከማሰር በመቆጠብ ብናከብራቸው በእጅጉ ያተርፉናል እንጂ አያከስሩንም ነበር፡፡

... የለውጥ መሰረቱ በግለሰቦች ውስጥ ያለ ነጻ ሐሳብ እና ያንን ሐሳብ በነጻነት መግለጽ መቻላቸው ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ነጻ ሐሳብ እንዳይፈጠር ወይም ከተፈጠረ በኋላ እንዲመክን ካደረከው፣ የምትቋምጥለት ለውጥ ከየት ተነስቶ፣ ምን ላይ ይቆማል? በግለሰብ ደረጃ እንዲጠፉ የተደረገ ነጻ ሐሳብ እንዴት ሆኖ በሕዝብ ዘንድ ይገኛል?

መታፈን ለሰው ባሕርይ የሚስማማ የማብሰያ ዘዴ አይደለም፡፡ ሰውን እንዲበስል ብለህ ብታፍነው አይበስልም... ይልቁንም ይጠነዛል፡፡ ሰው 'መኩክ' ብሎ የሚበስለው ነጻ መንፈሱን የሚመጥን ነጻነት ሲያገኝ እና ነጻ ሐሳቡን ማራመድ ሲችል ነው፡፡ የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የታሪክ እና የፖለቲካ ጓንት እያጠለቅህ ለምን ታፍነዋለህ?

ይህ ነው የነፍሴ ጩኸትና የመንፈሴ ሕመም፡፡ የሐሳቦቼ ማጠንጠኛም እሱው ነው፡፡ እርግጥ ነው በምሁራን፣ በጠቢባን፣

በፈላስፎች፣ በነገር እና በጨዋታ አዋቂዎች አገር መጽሐፍ ለማሳተም መነሳት ቀላል ውሳኔ አይደለም:: በውሳኔዬ ያጸናኝ ለሐሳብ ነጻነት ያለኝ ፍቅር እና ክብር ነው:: ደግሞ ከተቻለ፤ ከእነርሱ እንደ አንዳቸው መሆንን ማን ይጠላል?!

መልካም ንባብ!

# ማውጫ


የውርስ ግፍ (1)
ሕይወት እንቆቅልሽ (37)
47 (45)
አልተገናኘንም (51)
ከሬት የወጣ ማር (61)
ምንሽሮ (87)
ከጀርባ ያለው (101)
ሱቲ (113)
ቆቀሴማ (123)
የተሳከረ እውነት (135)
ኢትዮጵያ (147)
ጋሽ ሳጥናኤል (167)
ቆጠራው (185)
የወደቀው ጡት (191)
መውጫ (205)

ታሪኮቹ በደዘትነት ይበልጡኑ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ሕጸጾች ይጠንንባቸዋል። ከሕይወት ልምድ፣ አካባቢን ከማስተዋል እና ከንባብ የተወሰዱት መነሻ ሐሳቦች እንዲሁ አልተዘረፈጡም። ለአንዳንዶቹ ገጸ ባሕርያት እና ትልም ተዋቅሮላቸው አንጊ ታሪክ ሆነዋል። ሌሎቹ ደግሞ በምርጥ የቃላት አወቃቀርና ለዛ ቀልድ ተኳሽተው 'ወይ ግሩም!' የሚያስብሉ ተደርገዋል።

እንግዳወርቅ እንድርያስ
(ዲላ ዩኒቨርሲቲ፣ የሥነ ጽሑፍ መምህር)

በተለያየ የሥነ-ጽሑፍ ቅርፅና ሕብር የተቀነበበ ሥራ ነው። በጣም በስሏል፣ ደንድኗል። በጣምም ደስ ብሎኛል።

… ታሪኮቹ አጫጭር የሚባሉ፣ በምናብ (ልቦ-ለድ) እና በእውነታ (ኢ-ልቦለድ) የታጠሩ የባለ ብዙ የሕይወት ፈርጅ ጭምቅ-ነገር ናቸው። የተነሱት ጭብጦች እና የቋንቋ አጠቃቀሙ፣ የፈጠራ እና የማዋዛት ጥበቡ በንባብና አስተውሎት ስለመበልፀጉ ማመሳከሪያ ሆኖኛል።

ዘመዱ ደምስስ
(ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ የውጭ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሁፍ መምህር)

የተመጠነ እና ሥርዓት ያለው አነጋገር እንደሚባለው ሁሉ ለአጻጻፍ ቢባል የሚመጤት ነው። በነጻነት የማሰብ እምነቷን ለዛ በተላበሰ ቋንቋ ሳታታክት ታስተላልፋለች። በአንጉል 'ዘመናዊነትና ብልጽግና' ያልተበረዘውን እና ግርግር ያልበዛበትን - ከተፈጥሮ እና ግብርና ጋር የተቆራኘውን ገጠራማ እና መለስተኛ የገጠር ከተማዎች አኗኗር ታስናፍቃለች።

ከሁሉም በላይ የሀገራችን ነባራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ እና የማኅበረሰባዊ እሴቶቻችን መሸርሸር ያሳስቧታል፣ ያስጨንቋታል። ስለ ሀገሬ ግድ ይለኛል የሚል እና በሐሳብ ነጻነት የሚያምን ሁሉ ቢያነበው የሚያተርፍበት መጽሐፍ ነው።

ይኼ የልብወለዶች እና ወጎች ስብስብ የደራሲዋ የመጀመሪያ ሥራ መሆኑ ደግሞ ሥነ ጽሑፍ እጅግ ልታድግበት የምትችል ዘርፍ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ሮማን ተወልደብርሃን

Printing by Gola Publishing Service
+251 911 65 86 31

ዋጋ ብር 250
ዋጋ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር